| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | *"የክዳት ፡ ቀን ። "* |
| ደራሲ ፤ | ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፤ | ግንቦት ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንው ፥ ቀ፦.2011-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

## editorial | éditorial

## "የክዳት ፡ ቀን ። "

ግንቦት ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ ኢትዮጵያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በሽምጋይነት ፡ በቀረቧቸው ፡ ባሜሪካ ፡ መንግሥትና ፡ በግብር ፡ ዐበሮቹ ፡ ለንደን ፡ ላይ ፡ ተከዱ ። ይህች ፡ ቀን ፡ የክዳት ፡ ቀን ፡ ተብላ ፡ በታሪክ ፡ ስትታወስ ፡ ትኖራለች ።

ሽምግልና ፡ በባህላችን ፡ ክቡር ፡ ነው ። የክብረቱን ፡ መጠን ፡ ስንገልጥ ፡ *"ሰማይ ፡ ተቀደደ ፡ ቢሉ ፤ ሽማግሌ ፡ ይሰፉዋል!"* ፡ እንላለን ። ሰው ፡ ሌላን ፡ የሚያየው ፡ ራሱን ፡ በሚያይበት ፡ ዐይን ፡ ነውና ፥ አምነን ፡ ተከድተናል ፤ አይለምደንም ።

ከእንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከራሱ ፡ በቀር ፡ ሽምጋይ ፥ ካገሩ ፡ ወዲያ ፡ ጉዳይ ፡ አይኖረውም ። ችግራችንን ፡ ራሳችን ፡ እንፍታ ፤ ጠላትንም ፡ መግቢያ ፡ ቀዳዳን ፡ እንንሣው ።

ከቶ ፡ ችግራችን ፡ ምን ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ እስካኹን ፡ ለመፍታት ፡ ያቃተን ፥ ለጎምሳ ፡ ዓመት ፡ -- ፡ ለመቶም ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፡ -- ፡ ካልፈታነው ፥ አገሪቱ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ጠንካራ ፡ ሥርዐት ፡ ቢኖራት ፡ ይኾን ፡ እስካኹን ፡ ያልፈራረሰችው ፥ የችግሩስ ፡ መነሻ ፡ ምን ፡ ይኾን ፥ ከውስጥ ፡ የመነጨ ፡ ወይስ ፡ ከውጭ ፡ የተቈሰቈሰ ፥ ወይስ ፡ ከኹለቱም ፥ ስለችግሩ ፡ ምንነት ፡ ስንመራመር ፥ ብዙዎቻችን ፡ የደረስንበትን ፡ ጭብጥ ፡ ስም ፡ ሳናወጣለት ፡ ኖረን ፥ ዛሬ ፡ *"ንኊልዮሽ"* ፡ ወይም ፡ *"nihilism"* ፡ ወደሚለው ፡ ልየታ ፡ አምርተን ፥ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ስምምነትን ፡ አግኝተናል ። ንኊልዮሽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ያልተወሰነ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ተረማምዶና ፡ ተዛምቶ ፥ ጥንታውያን ፡ ሥልጣኔዎችን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ የተፈታተነ ፡ አጥፊ ፡ ኀይል ፡ ነው ። ከመንግሥታት ፡ ጥቂቶቹን ፡ እንደ ፡ ዩጎስላቪያ ፡ ሲደመስሳቸው ፥ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያሉትን ፡ ገፍትሮ ፡ ቢጥላቸውም ፥ አላሸነፋቸውም ። እንደ ፡ ቻይና ፡ ያሉቱ ፡ ደግሞ ፥ *"በተረቱበት ፡ ይረቱበት ፤ በተመቱበት ፡ ይመቱበት"* ፡ እንዲሉ ፥ የመጣባቸውን ፡ ዐጥፊ ፡ ኀይል ፡ በኀይልነቱ ፡ ገርተውና ፡ ጨብጠው ፡ ይዘው ፡ ተቋቁመውታል ። የባሰ ፡ ቢመጣባቸው ፥ ብቻቸውን ፡ እንደማይጠፉ ፡ አረጋግጠዋል ።

ሀገር ፡ ከወደቀበት ፡ የሚነሣው ፡ ቀድሞውኑ ፡ በቆመበት ፡ ሥልጣኔው ፡ ነውና ፥ ኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ አገባብ ፡ በሥልጡንሕዝብናዋ ፡ ዳግመኛ ፡ ተነሥታ ፡ ትቆማለች ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።